# ቡጡቡጥ ፣ ጫጫታ

በአንድ ወቅት ክሩቼቭ የአሳማ ርባታ በረትን ከጎበኙ በኋላ ለመታሰቢያ ይሆን ዘንድ ብሎ ከአሳሞቹ መሀል ሆኖ ፎቶ ይነሳል። በማግስቱ ለሚወጣው ጋዜጣ ምድረ ጋዜጠኛ ከቢሯቸ ው ተሰብስበው ከፎቶው ሥር የሚያጅበውን ቃላት በመምረጥ ሥራ ተጠምደዋል።

አንዱ ተነስቶ እንዲህ ይላል ፥ ጓድ ክሩቼቭ በአሳሞች መሀል፣
ሌላው ደግሞ በማሻሻል መልክ ፣ ጓድ ክሩቼቭና አሳሞች ሲል፣
ሌላው ጋዜጠኛ ቀበል ያደርግና በጓድ ክሩቸቭ ዙርያ ያሉ አሳሞች ይላል።
በዚህ ጊዜ ብስጭት ያለው ዋና ኤዲተር ፣ የራሱን ውሳኔ ይወስናል እንዲህ ሲል። ከበስተግራ በኩል ያሉት ሶስተኛው ጓድ ክሩቼቭ ናቸው ።

ሰሞኑን በወያኔውች ዙርያ ለተፈጠረው የቆሌ አለመረጋጋት በውጥረት ዘመን አረጋጊ መሀንዲስ ናቸው ተብለው በህዉሀት መንደር የሚታወቁት፣ እሳቸው እንዳሉት በቡና ረከቦት ላይ ያውም ጾረና ላይ አቦይ ስብሀት ተብሎ ስም የወጣላቸው ሰው በተለያየ መድረክ የሰጡትን ቃለ መጠይቅ አድምጠናል።
ቡና አፍሊዋ የትግራይ ሴት ከሰው መንደር ኤርትራ ያውም ጾረና ለአቦይ የስኒ መቀመጫ ገልብጣ፣ ወይም የፍየል ሞራአንብባ ያወጣችላቸው ስም ግን አቦይን አቦይ አላደረጋቸውም ። እንዳመጣላቸው የሚናገሩት አቦይ ልክ እንደክበበው ገዳ ኮሜዲ ቪድዮ ፥ *ቡጡቡጥ ፣ ጫጫታው ገብረ መድህን* ጮምላቃ፣ሾርሙጣ አይነት፥ጡሩግ፡ በሉ፣ ሙናባታቹ፣ገበጣ ህዝቢ፣ያበሳበሰው ንብረት፣ ሲሉ ተደምጠዋል።

የህውሀት መሪዎች ሁሉም በአሳሞች መሀል ስለሚገኙ ቢያንስ እንኳ የሚወክሏትን አገርና ስም እንዲሁም ክብር ለማስጠበቅ እንኳ የተሞረደ ቋንቋ አይጠቀሙም። በዚያን ክፍፍላቸው ወቅት ፣ ከፍተኛው ቱባው መሪያቸው በአደባባይ ለርእሰ መሪ በማይመጥን ቋንቋ ..የበሰበሱ..የበሸቀጡ.. ሲሉ ህዝቡ ቴሌቪዥኑን ያጠፋ ነበረ አሉ ። ነግ በኔ ብለው ልጆቻቻው ስድብ እንዳይማሩ ።

በቪኦኤ አቦይ ገና አፋቸውን ሲከፍቱ ቮይስ ኦፍ አሜርካ የተቃዋሚዎች በረት ነው ሲሉ ተደምጠዋል። በረት ነው ያሉትን ቤት ግን እሳቸውም ተገኝተውበታል።ወያኔዎች አዲስ አበባ የገቡ ዘመን ፣ አፈር ይቅለለውና ጳውሎስ ኞኞ ቤተመንግስቱንና ምክር ቤቱን በበሬቶ ሲሙነሽነሹበት አይቶ አንድ የተናገራት ቀልድ ነበረች አሉ አሁን ጠፍታኛለች።

አቦይ ምን ያልገለጠጡት ነገር አለ? …በበረባሶ ጫማ ሸገር የገባው አፍሮ ወያኔ ለካ ከተሜዎችን አጃጅሎ ነበር ቺስታ መስሎ ። አይ የከተሜ ልጆች ! አራዳ ነን ስትሉ ወረዳ ሆናችሁ አይደል ፤

በቁምጣ ብገባ አስጥፌ ጠቁሜ፣
ቺስታ ነው አለችኝ ያች ሞኝ ከተሜ፣
መርከቤን አላየች ህንጣና ሆቴሉን፣
ሎንዶንና ሳውዲ ዲሲ ዋሽንግቶን።
ሁሉም የህዉሃት ሙናአባትክ ትሆን

የሚል ነጠላ ዘፈን እለቃለሁ እያሉ ነው አሉ አቦይ ከዲሲ!! ቁርጡን ንገሪኝ…ቁርጡን..ንገሪኝ እያለ የሚዘፍነው ማን ነበር እናንተዬ?አቦይ እኮ ቁርጡን ነግረውናል። የቡርዣ አብዮት እያካሄድን ስለሆነ፣ እኔም ዋሽንግቶን ስለካፒታሊዝም ትምህርት ለመቅሰም ስለመጣሁ፣ ካፒታሊዝም The higest stage ላይ ኢትዮጵያ ላይ ሲደርስ ያኔ ወያኔ ያከስማል እስከዚያ እስከ ልጅ ልጅሽ ሀወሀት ይገዛል አራት ነጥብ ብለውናል።

ክቡር አቶ  ስብሀት ትክክል ብለዋል!! ታላላቅ ግዙፍ ሀብቶች በኢትዮጵያ የህውሀት ስለሆኑ፣ የሚያተርፉትም ሆነ ቋሚ ካፒታላቸው ባለቤት የትግራይ ህዝብ ስለሆነ ወደዳችሁም ጠላችሁም እኔም ወደላይኛው ቤት ለመሄድ መንገድ ላይ ብሆንም ልጅ ልጆቻችን ግን ይገዙዋችኋል እያሉን ነው ያሉት። በዚህ ደግሞ ያልተስማማ ወይ አብሲት ጥዶ የመጣ፣አሊያም ደጃፉን ሳይዘጋ የመጣ ሰው ካለ እንደ ገብረመድህን አባባል ጡሩግ በሉ ሙናባቱ መገንጠል መብታችን ነው ሊሉን ነው።

ዋኣ ! አይታ መምሬ አለ ገብረመድህን!! ዋኣ ! አቦይ ስብሀት አንድ ግርም የሚል የተደበቀ ነገር አሰሙን። ያ ! ደርግ ለካ የተገነጠለች ኤርትራን ነበር  ለወያኔ ያስረከበው ? እነ አቦይ ማህተም ብቻ እንዳሰፈሩ  እንጂ ኤርትራን እንዳላስገነጠሉ አስረግጠው ነግረውናል።የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነበር ሲሉ ያሰፈሩትንም የህዉሀት ማንፌስቶ ባንዴ ሽረው ለሌላ አካል ሰጥተውታል። ምን ችግር አለ ከአልባንያ ኮሚንዝም ወደ ቡርዧ አብዮትስ ባንዴ ተገልብጣችሁ የለ?

ይሄ ወያኔ ሃርነት ትግራይ የሚሉት ክፍል ያሰባሰበው ሰው ሁላ የአይምሮ ልክፍት የሚያጠቃውን ብቻ ነው? አንዱ ሸምጣጭ ቁጭ በሉ፡አንዱ ደግሞ ዘገምተኛ አንጎል ያለው።
Pathological liars have little regard or respect for the rights and feelings of others. They often come across as being manipulative, cunning and self-centered. Nonetheless, if combined with sociopathic tendencies, they can be charming and superficially extremely likable people. እንዲህ እያለ ስለቁጭበሉዎቹ መጥሃፉ ሲናገር  ለቅዠታሞቹ **Dementia** ችግር ላለባቸው ደግሞ እንዲህ ይላቸዋል።
Symptoms of dementia vary depending on the cause and the area of the brain that is affected. Memory loss is usually the earliest and most noticeable symptom.

በመጨረሻው የማሳረጊያው ንግግርዎ ወቅት የናገሩትን ንግግር ግን ወድጄልሆታልሁ ። በኢትዮጵያ ታሪክ በመንግሥት ላይ ያልተቆጣ ህዝብ የታየው በኢሃዴግ  ግዜ ነው ያሉት። ላመለክት ነው  ለዚህ ታላቅ ፓርቲ አባልነት።አባባልዎት ወደ ቀድሞዋ ሶቭየት ኅብረት ጊዜ ቀልድ ወሰደኝ።
አንድ  ኢቫኖቭ የሚባል ሰው ለኮሚንስት ፓርቲ አባልነት ጥያቄ ያቀርባል። የፓርቲው የምልመላ ክፍል  ሀላፊ  ለኢቫኖቭ ከዚህ የሚከተለውን ጥያቄ ያቀርብለታል።

ጓድ ኢቫኖቭ፥ ታጨሳለህ ?
አዎ በትንሹ
አታውቅም? ጓድ ሌኒን እንደማያጨሱ እና ሌሎችም እንዳያጨሱ ሲመክሩ?
ጓድ ሌኒን እንዲህ ካሉማ ማጨሰኔ አቆማለሁ።
ጓድ ኢቫኖቭ ትጠጣለህ ?
አዎ በትንሹ ፣
ጓድ ሌኒን መጠጣትን በጽኑ ያወግዛሉ
ካወገዙማ መጠጣቴንም ባስቸኳይ አቆማለሁ
ጓድ ኢቫኖቭ ሴትስ ትወዳለህ?
በትንሹ
አታውቅም ጓድ ሌኒን ሞራል ስለሌላቸው ዝሙተኞች የተናገሩትን?
ጓድ ሌኒን መውደድን ካወገዙማ ሴት በዞረችበት አልዞርም።
ጓድ ኢቫኖቭ ለመሆኑ ለዚህ ፓርቲ ራስህን መስዋዕት ለማድረግ ተዘጋጅተሀል?
"Of course. Who needs such life?"

አቦይ ኢህአዴግ አሳቀኝ።

እንግዳ / ከኖርዌ